**መመሪያ ቁጥር 231/2013**

# በማስተላለፊያ ዋጋ የሚደረግ ግብይትን ለመከላከል የወጣ መመሪያ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የገቢ ግብር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 286/1994) በአንቀጽ 29 በተመለከተው መሠረት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የሚደረጉ ግብይቶች የገበያ ዋጋ መርህን ተከትለው መካናወን ስላለባቸው፣

ዓለም አቀፍ ሚልካም ተሞክሮዎችን (በተለይም ደግሞ የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትብብር ድርጅት የማስተላለፊያ ዋጋ መመሪያዎችን) መሠረት ያደረገና የገበያ ዋጋ መርህን ሥራ ላይ ለማዋል የሚጠቅም፣ ሁሉን አቀፍ የሆነ በማስተላለፊያ ዋጋ የሚደረግ ግብይትን ለመከላከል የሚያስችል አሠራር ማዘርጋት በማስፈለጉ፣

በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 29(1) ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ መ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በማስተላለፊያ ዋጋ የሚደረግ ግብይትን ለመከላከል የወጣ መመሪያ ቁጥር 231/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች ከዚህ በታች የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

1. "የሚፃፀሩ ግብይቶች" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 መሠረት ሊነፃፀሩ የሚችሉ ግብይቶች ናቸው፡፡
2. "ቁጥጥር የተደረገበት ግብይት" ማለት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ማንኛውም ግብይት ነው፡፡
3. "የሀገር ወስጥ ግብይት" ማለት በታክስ ከፋዮች መካከል በአገር ወስጥ የሚደረግ ማንቸውም ግብይት ነው፡፡
4. "የተግባር ትንተና" ማለት ዋጋ ያለወን ንብረት እና ሊደርስ የሚችለወን አደጋ ታሳቢ በሚድረግ ስለግብይቶች የሚለጽበት ትንተና ነው፡፡
5. "የገቢ ግብር አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገቢ ግብር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 286/1994) ነው፡፡

6. "ዓለም አቀፍ ግብይት" ማለት በታክስ ከፋይና ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ ባልሆነ ሰው መካከል የሚደረግ ግብይት ነው፡፡

7 "ነዋሪ ያልሆነ" ማለት በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ነው፡፡

8. "ሰው" ማለት በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 2(1) ሥር እንደተደነገገው ማንኛውም ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም የሰዎች ህብረት ነው፡፡

9. "ግንኙነት ያላቸው ሰዎች" የሚለው በገቢ ግብር አዋጅ 2(4) የተሰጠው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

10. "ነዋሪ" ማለት በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 5 ሥር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

11. "የታክስ ባለስልጣን" ማለት የፌደራል ወይም የክልል የታክስ ባለስልጣን ነው፡፡

12. "ታክስ ከፋይ" ማለት በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 2(7) የተሰጠውን ትርጉም የሚይዝ ነው፡፡

13. "ታክስ የሚከፈልበት ገቢ" በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 2(11) የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

14. "መክራ የተደረገበት ሰው" ማለት ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ወስጥ ተሳታፊ የሆነ የፋይናንስ ጠቋሚው የሚለሰ የመሸጫ ዋጋ፣ የተጨማሪ ወጪ እና የግብይት የተጣራ ትርፍ ዘዴዎችን በመጠቀም መክራ የተደረገበት ይሆናል፡፡

15. "ግብይት" ማለት

- ሀ) የዕቃዎች ግዢና ሽያጭ፣
- ለ) ተጨባጭነት (ግዙፋዊ ህልዮት) ያላቸውን ዕቃዎች፣ የካፒታል ዕቃዎችንም ጨምሮ) የመግዛት፣ መሸጥ፣ ማከራት ወይም መጠቀምን፣
- ሐ) ግዙፋዊ ህልዮት የሌላቸውን ሀብቶች መግዛት፣ መሸጥ፣ ማከራየት ወይም መጠቀምን፣
- መ) የአገልግሎቶችን አቅርቦት፣
- ሠ) የፋይናንስ አቅርቦትና ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን፣
- ረ) ሌላ ማናቸውም ግብይት፣ ወል፣ ግንኙነት፣ የተጻፈ ቢሆንም ባይሆንም፣ የታክስ ከፋዩን ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ሊነካ የሚችል ማንኛውም ግብይት ነው፡፡

16. "ቁጥጥር ያልተደረገበት ግብይት" ማለት ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ማንኛውም ግብይት ነው፡፡

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 29(1) በተመለከተው መሠረት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ማንኛውም ዓለም አቀፍ እና አመታዊ ገቢያቸው ከ500,000 ብር በላይ በሆኑ ግንኙነት ባላቸው ግብር ከፋዮች መካከል በሚደረግ የሀገር ወስጥ ግብይት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. <u>የገበያ ዋጋ መርህ</u>

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ ግንኙነት ካለው ሰው ጋር ግብይት በሚፈጽምበት ጊዜ ታክስ የሚከፈልበት ገቢውን የሚወስነው ከገበያ ዋጋ ሚዛን ጋር በተጣጣመ መልኩ መሆን አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ከገበያ ዋጋ ሚዛን ጋር የተጣጣመ ነው የሚባለው በዚህ ግብይት ያሉት ሁኔታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በሚደረጉ ግብይቶች ወስጥ ከሚገኙት ሁኔታዎች ጋር ያልተለየ የሆኑ እንደሆነ ነው፡፡

3. ቁጥጥር የተደረገባቸው ግብይቶች ከገበያ ዋጋ ሚዛን ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውና ማቸውም የዋጋ ማስተካከያ ማጠን የሚወሰነው በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡

## 5. ተነፃፃሪነት

1. አንድ ቁጥጥር ያልተደረገበት ግብይት ቁጥጥር ከተደረገበት ግብይት ጋር ተነጻጻሪ ነው የሚባለው፡ –

   ሀ) አግባብነት ባለው የማስተላለፊያ ዋጋ መወሰኛ ዘዴ መሠረት የሚዛሚዛውን የፋይናንስ ጠቋሚ ትርጉም ባለው መልኩ በሚይነካ ሁኔታ በሁለቱ ግብይቶች መካከል ልዩነቶች የሌሉ እንደሆነ፣

   ለ) ልዩነቶች ቢኖሩ እንኳን፣ ልዩነቶቹ በንፅፅሮቹ ላይ የሚያስከትሉትን ወጤት ለማስወገድ ትክክለኛ የንጽጽሮሽ ማስተካከያ አብባብነት ባለው ቁጥጥር ባልተደረገበት ግብይት የፋይናንስ ጠቋሚ ላይ ተደርጎ ልዩነቶች የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡

2. ግብይቶቹ ለተፈፀሙበት ሁኔታ ኢኮኖሚያዊ አግባብነት እስካላቸው ድረስ ሁለት ግብይቶች የሚጻጸሩ ናቸው ብሎ ለመወሰን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከግምት ወስጥ ይገባሉ፡ –

   ሀ) የንብረቱ ወይም የአገልግሎቱ ባህሪይ፣

   ለ) ግብይቱን አስመልክቶ በእያንዳንዱ ሰው የተከናወነው ተግባር፣ ጥቅም ላይ የዋለው ንብረት፣ የተጋረጠው ስጋት፣

   ሐ) የግብይቶች የወል ቃላትና የወል ሁኔታዎች፣

   መ) ግብይቶች የተከናወኑባቸው የኢኮኖሚ የገበያ ሁኔታዎች፣ እና

   ሠ) ግብይቶቹን የፈፀሙ ሰዎች የሚከተሏቸው የንግድ ስልቶች፣

3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) አፈጻፀም የንጽጽሮሽ ማስተካከያ የሚደረገው የወጤቱን አስተማማኝነት ለመጨመር ሆኖ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ግምት ወስጥ በማስገባት ነው፡፡

   ሀ) ማስተካከያው የሚደረግበት ልዩነትና ወሳኝነት፣

   ለ) ማስተካከያ የሚደረግበት የመረጃ ጥራት፣

   ሐ) የማስተካከያው ዓላማ፣

   መ) ማስተካከያው የሚደረግበት ዘዴ አስተማማኝነት

## 6. በማስተላለፊያ ዋጋ ግብይት ያለመፈፀማ ለሚጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዘደዎች

1. ለዚህ መመሪያ አፈጻፀም ሲባል የሚተላለፊያ ዋጋ ግብይት ያለመኖሩን ለሚረጋገጥ የሚከተሉት ዘዴዎች ጥቅም ላይ ይወላሉ፡፡

ሀ) ቁጥጥር ያልተደረገበት ተነጻጻሪ ዋጋ ዘዴ፡- ይህ ዘዴ ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ወስጥ ለንብረት ወይም ለአገልግሎት የተከፈለወን ዋጋ ቁጥጥር ባልተደረገበት ግብይት ለንብረት ወይም ለአገልግሎት ከተከፈለው ዋጋ ጋር የሚጻጸርበት ዘዴ ነው፡፡

ለ) ሚሉሰ የሚሻጫ ዋጋ ዘዴ፡- ይህ ዘዴ አንድ ሰው ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት የገዛወን ዕቃ ቁጥጥር ባልተደረገበት ግብይት በመሸጥ ያገኘወን ትርፍ በሌሎች ቁጥጥር ባልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶች ተመሳሳይ ዕቃ ተሸጦ ከሚገኘው ትርፍ ጋር የሚጻጻርበት ዘዴ ነው፡፡

ሐ) የተጨፄሄ ወጪ ዘዴ፡- ይህ ዘዴ ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ወስጥ ንብረቶችን ወይም አገልግሎቶችን ለመቅረብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የወጡት ተጨፄሄ ወጭዎች ቁጥጥር ባልተደረገባቸው ግብይቶች ንብረቶችን ወይም አገልግሎቶችን ለመቅረብ ከወጡት ወጭዎች ጋር የሚጻጸሩበት ዘዴ ነው፡፡

መ) የግብይት የተጣራ ትርፍ (Transaction net margin) ዘዴ፡- አንድ ግብይት የፈጸመ ወገን ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ወስጥ ተገቢ የሆነ አንጻራዊ መሠረት (ለምሳሌ ወጭዎች፣ ሽያጮች፣ ንብረቶች) ላይ ተመስርቶ የሚገኘው የተጣራ ትርፍ ቁጥጥር ባልተደረገበት ተነጻጻሪ ግብይት ወይም ግብይቶች ወስጥ ተመሳሳይ በሆነ አንጻራዊ መሠረት ላይ ተመስርቶ ከሚገኘው የተጣራ ትርፍ የሚነፀርበት ዘዴ ነው፡፡

ሠ) የግብይት ትርፍን የሚከፋፈል (transaction profit split) ዘዴ፡- ይህ ዘዴ አንድ ግንኙነት የሌለው ሰው ቁጥጥር ባልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶች በመካተፍ የሚጠበቀወን ትርፍ (ከሰራ) ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ወስጥ ተሳትፎ ላደረገ ግንኙነት ላለው ለእያንዳንዱ ሰው የሚደለደልበት ዘዴ ነው፡፡

በዚህ ንዑስ አንቀጽ ሀ-መ የተገለጹትን ዘዴዎች በማጠቀም በአንድ ወይም በሁለት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች የተከናወኑ የተወሰኑ ተግባራት የገበያ ዋጋ የተከተሉ መሆናቸወን መወሰን የማቻል ከሆነ፤ለእነዚህ ተግባራት ክፍያ ሲፈጸም የሚጣወን ቀሪ የጋራ ትርፍ (ከሰራ) መሠረት በማድረግ የግብይት ትርፍን የሚከፋፈል ዘዴ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም አንድ ታክስ ከፋይ በሚተላለፊያ ዋጋ ግብይት ያለሚፈፀማ ለሚረጋገጥ ጥቅም ላይ ከሚውሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተፈቀዱ ዘዴዎች ወጪ ሊጠቀም የሚችለው በተፈቀዱት ዘዴዎች የትኛዉም ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ወስጥ ያለወን የገበያ ዋጋ ለመወሰን የሚችሉ ሲሆን እና ታክስ ከፋዩ የሚጠቀመው ሌላ ዘዴ የሚያመጣው ወጤት ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የሚጣጣም ሲሆን ነው፡፡

## 7. <u>በሚተላለፊያ ዋጋ ግብይት ያለሚፈፀማ ለሚረጋገጥ የተመረጡ ዘዴዎች አጠቃቀም</u>

1. ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት የሚሄዩት ሁኔታዎች ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸው የሚወሰነው የበለጠ ተገቢ የሆነወን ዘዴ ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ሥር ከተመለከቱት ዘዴዎች መካከል የበለጠ ተስማሚ የሆነው የሚመረጠው የሚከተሉት መስፈርቶች ከግምት ወስጥ ገብተው መሆን አለበት፣

ሀ) የእያንዳንዱ ዘዴ ተነጻጻሪ ጥንካሬና ደካማ ጎን፣

ለ) ቁጥጥር ከተደረገበት ግብይት ባህሪይ አንጻር ተቀባይነት ያገኘው ዘዴ አግባብነት ግምት ወስጥ የሚገባው እያንዳንዱ ወገን ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ምን ተግባር እንዳከናወነበት ትንተና በማድረግ፣ (የተከናወኑት ተግባራት፣ ጥቅም ላይ የዋሉት ንብረቶች እና የተደቀነው ስጋት ትንተና)

ሐ) የተመረጠዉን ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቅም አስተማማኝ መረጃ መኖሩ፣

መ) ቁጥጥር በተደረገበትና ቁጥጥር ባልረደረገበት ግብይት መካከል ያለው የንጽጽሮሽ ማጠን፣ በሁለቱ የግብይት ዓይነቶች መካከል የሚኖረዉን ልዩነት ለማስወገድ የሚፈለገው የንጽጽሮሽ ማስተካከያ አስተማማኝነትንም ጭምር፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ያሉት መስፈርቶች ግምት ወስጥ ገብተው፣ በአንቀጽ 6(1(ሀ) እና(ለ) በአንቀጽ 1(ለ) ሥር የተዘረዘሩት ዘዴዎች በእኩል አስተማማኝነት ደረጃ ተግባራዊ የሚሆኑ ከሆነ በአንቀጽ 6(1(ሀ) የተመለከተው ዘዴ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከቱት መስፈርቶች ግምት ወስጥ ገብተው በአንቀጽ 6(1(ለ-ሐ) ከተመለከቱት ዘዴዎች አንዱ እና በአንቀጽ 6(1(መ-ሠ) ከተመለከቱት ዘዴዎች ወስጥ አንዱ ከሌላው ጋር በእኩል ደረጃ አስተማማኝ ከሆኑ በአንቀጽ 6(1(ለ እና ሐ) የተመለከተው ዘዴ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

4. የአንድ ቁጥጥር የተደረገበት ግብይት ሁኔታዎች ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸዉን ለመወሰን ከአንድ በላይ የማነፃፀሪያ ዋጋ ዘዴ ማጠቀም አይቻልም፡፡

5. የታክስ ባለስልጣኑ ተግባራዊ የሆነው ዘዴ የበለጠ አግባብነት የሌለው መሆኑን ያረጋገጠ ካልሆነ በስተቀር፣ ማንኛዉም ታክስ ከፋይ ተቀባይነት ያገኘዉን ዘዴ ተጠቅሞ ሲገኝና የዘደው አመራረጥ ከዚህ አንቀጽ ጋር የተጣጣመ ሆኖ ሲገኝ ቁጥጥር በተደረገበት የታክስ ከፋዩ ግብይት ወስጥ ያሉት ሁኔታዎች ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸዉን የታክስ ባለስልጣኑ ምርመራ በሚያደርግበት ጊዜ በታክስ ከፋዩ የተመረጠው ዋጋ ዘዴ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## 8. <u>መከራ የሚደረግበት ሰው ስለማሪጥ</u>

መከራ የሚደረግበትን ሰው የማምረጡ ሂደት የተጨማሪ ወጪ ሜሎ የመሻጫ ዋጋ ወይም በግብይት የተጣራ ትርፍ ዘዴዎች ተፈፃሚ በሚሆኑበት ጊዜ ከግብይቱ የተግባር ትንተና ጋር ወጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 9. <u>ቁጥጥር የተደረገባቸው ጥምር ግብይቶችን ማምገም</u>

አንድ ታክስ ከፋይ በተመሳሳይ ሁኔታዎች አንድ ወይም ከዚህ በላይ የሆኑ ቁጥጥር የተደረገባቸው፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ያላቸው እና ለየብቻቸው በአስተማማኝ ሁኔታ ሊተነተኑ የሚችሉ ግብይቶች ያደረገ እንደሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተመለከተዉን የንጽጽሮሽ ተግባር ለማከናወንና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የማስተላለፊያ ዋጋ ስሌት ዘዴዎች ተግባራዊ ለማድረግ እነዚህ ግብይቶች ሊጣምሩ ይችላሉ፡፡

## 10. <u>የገበያ ዋጋ ህዳግ</u>

1. የገበያ ዋጋ ህዳግ የሚወሰነው አግባብነት ያላቸዉን የፋይናንስ ጠቋሚ ቁጥሮች (ለምሳሌ ዋጋዎች፣ ህዳጎች ወይም የትርፍ ድርሻዎች) መሠረት በማድረግ ሆኖ ወጠቱ የሚገኘዉም በጣም

የተሻለውን የማስተላለፊያ ዋጋ ስሌት ዘዴ (በአንቀጽ 7 መሠረት) በጣም በርካታ ለሆኑና በአንቀጽ 5 መሠረት የንጽጽሮሽ ትንተና በተደረገባቸውና ቁጥጥር ባልተደረገባቸው ግብይቶች ላይ ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡

2. ቁጥጥር የተደረገበት ግብይት ወይም ደግሞ በአንቀጽ 9 መሠረት የተጣመሩ ግብይቶች በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 29 መሠረት ማስተካከያ የሚደረግባቸው፣ ቁጥጥር ከተደረገበት ግብይት ወይም ልዩ ልዩ ግብይቶች የሚገኘው የፋይናንስ ጠቋሚ ከገበያ ዋጋ ህዳግ ያልበለጠ እንደሆነ ነው፡፡

3. አግባብነት ያለው ቁጥጥር የተደረገበት ግብይት ወይም በአንቀጽ 9 መሠረት የተጣመሩ ግብይቶች የፋይናንስ ጠቋሚ ከገበያ ዋጋ ህዳግ ውጭ የሆነ እንደሆነ የታክስ ባለሥልጣኑ በገቢ ግብር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 286/1994) አንቀጽ 29(1) መሠረት የዋጋ ማስተካከያው ማሳያ አድርጎ የሚወስደው የገበያ ዋጋ ህዳግን አጋማሽ ቁጥር ነው፡፡ ነገር ግን ታክስ ከፋዩ ወይም የታክስ ባለሥልጣኑ በህዳጉ ወስጥ ሌላ ነጥብ የበለጠ ተስማሚ መሆኑን ማሳየት ከቻሉ የህዳጉ አጋማሽ ቁጥር ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 አፈጻፀም ሲባል የገበያ ዋጋ ህዳግ አጋማሽ ቁጥር ተደርጎ የሚወሰደው የገበያ ዋጋ ህዳጉን ካስከተሉት ቁጥጥር ከተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶች የሚገኘው የፋይናንስ ጠቋሚ ቁጥር 50ኛው ፐርሰንታይል ነው፡፡ ለዚህም ዓላማ ሲባል 50ኛው ፐርሰንታይል የሚባለው የፋይናንስ ጠቋሚው አነስተኛው ቁጥር ሆኖ ቢያንስ የፋይናንስ ጠቋሚው ቁጥር የቁጥሩ ወይም ከቁጥሩ በታች 50% ሲሆን ነው፡፡ ሆኖም ግን ከወጤቶቹ 50%ቱ ከፋይናንስ ጠቋሚው ቁጥር ጋር እኩል ወይም ከዚያ በታች ከሆኑ ፐርሰንታይሉ ከአማካይ ወጤቱ እና ከዚያ ከሚበልጠው ቁጥር ጋር እኩል ይሆናል፡፡

5. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 እና 16 እንደተጠበቁ ሆነው፣ በገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ 29(1) መሠረት የዚህን አንቀጽ ንዑስ 3 መሠረት በማድረግ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ማስተካከያው ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፍልበትን ገቢ እንዲጨምር የሚያደርግ እንደሆነ ነው፡፡

## 11. <u>ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶችን የሚመለከቱ የመረጃ ምንጮች</u>

1. ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ተነፃፃሪ ግብይቶችን አስመልክቶ የሚከተሉት የመረጃ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ፡ -

   ሀ) ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ወስጣዊ ግብይቶች ማለትም ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ግብይቶች ሆነው ቁጥጥር በተደረገባቸው ግብይቶች ተዋዋይ ወገን የሆነው ቁጥጥር ባልተደረገባቸው ግብይቶችም ተዋዋይ ወገን ሆኖ ሲገኝ፡፡

   ለ) ውጫዊ ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ግብይቶች ማለትም ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ግብይቶች ሆነው ቁጥጥር በተደረገባቸው ግብይቶች ተዋዋይ ወገኖች ከሆኑት ሰዎች ወስጥ አንዳቸውም ተዋዋይ ወገኖች ያልሆኑባቸው ግብይቶች ናቸው፡፡

2. ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ውጫዊ ተነጻጻሪ ግብይቶችን የሚመለከት መረጃ በገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ 29(1) መሠረት የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ ለታክስ ባለሥልጣኑ እንደማሳያ ሆኖ

የሚገለግለው ግብይቱን የሚመለከት ሚረጃ በታክስ ከፋዩ አማካይነት ለታክስ ባለሥልጣኑ እንዲደርሰው ያልተደረገ እንደሆነ ነው፡፡

3. ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶችን የሚመለከት መረጃ በታክስ ከፋዩ አማካይነት ለታክስ ባለሥልጣኑ እንዲደርሰው ያልተደረገ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ አንድ ግብይት ከገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ 29 ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማስረዳት ይህንን መረጃ እንደ ድጋፍ (ማሳ) ሊጠቀምበት አይችልም፡፡

4. በአንድ ተመሳሳይ አካባቢያዊ ገበያ (ማለትም ሀገር ወይም ክልል) ቁጥጥር ያልተደረገባቸውን ግብይቶች ቁጥጥር ከተደረገባቸው ግብይቶች ጋር ለማነጻጸር የሚረዳ መረጃ ያልተገኘ እንደሆነ በሌላ አካባቢያዊ ገበያ የተደረጉ ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶች በታክስ አስገቢው ባለሥልጣን ተቀባይነት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ከሌሎች አካባቢ ገበያዎች የተገኙ ተነጻጻሪዎች አስተማማኝነት
ከእያንዳንዱ ጉዳይ አንጻር እየተመዘነ የሚወሰን ሲሆን፣ እነዚህ ተነጻጻሪዎች በአንቀጽ 5 የተመለከቱትን ማስፈርቶችን በሚያሟሉት ልክ (መጠን) እና ለንጽጽሩ የሚረዱ መረጃዎች የመገኘታቸውን መጠን መሳሻ በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን ተነጻጻሪዎች የሚጠቀሙ ታክስ ከፋዮች በተቻለ መጠን በዋጋና በትርፍ ላይ የሚጠበቀውን አካባቢያዊ ተፅዕኖ በሚገባ ማገምገም ይኖርባቸዋል፡፡

12. **የግብይት ዋጋ የመወሰኛ ዘዴን አስቀድሞ ማስማማት**

1. የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 29(2) እንደተጠበቀ አንድ ግብር ከፋይ በተወሰነ ጊዜ ወስጥ የሚከናወን ቁጥጥር የሚደረግበት ግብይት በገበያ ዋጋ መርህ እንዲመራ ሚድረግ የሚያስችሉ ማስፈርቶችን በማዘጋጀት ከታክስ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጋር በግብይት ዋጋ መወሰኛ ዘዴ ላይ አስቀድሞ ስምምነት እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚደረግበት ጊዜ በሚኒስትሩ በሚተላለፍ ሠርኩላር ይወሰናል፡፡

2. የግብይት ዋጋ የመወሰኛ ዘዴን አስቀድሞ በሚደረግ ስምምነት ለመወሰን የሚቀርብ ጥያቄ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፡፡

   ሀ. የግብር ከፋዩን የሥራ ዓይነት፣ ቁጥጥር የሚደረግበትን ግብይት ዓይነት እና የስምምነቱ ረቂቅ የተፈፃሚነት ወሰን እና የሚቆይበትን ጊዜ፣

   ለ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተመለከተውን የገበያ ዋጋ መርህ ተከትሎ በግብር ከፋይ የሚቀርብ የስምምነት ረቂቅ በአንቀጽ 5 መሠረት ለጉዳዩ ወሳኝ ናቸው የሚባሉትን የማነፃፀሪያ ማስፈርቶች በአንቀጽ 6 ከተመለከቱት መካከል ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የሚስተላለፊያ ዋጋ ዘዴን እና የመወሰኛ ዘዴውን ለማሟረጥ ወሳኝ የሆኑትን ግምቶች፣

   ሐ. ግብር ከፋዩ በዚህ ስምምነት ወስጥ ሊካተት የሚፈልገውን አገር/አገራት እና

   መ. በታክስ ባለሥልጣን መ/ቤቱ እንዲቀርቡ የሚጠየቁ ማናቸውንም መረጃዎች

3. የታክሱ ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ሊያሟላ የሚችል መሆኑን እና ከዚህ ስምምነት የሚገኘውን ጥቅም ከግምት ወስጥ በማስገባት ታክስ ከፋዩ ባቀረበው ጥያቄ ላይ ወሳኔ ይሰጣል፡፡ በቂ ምክንያት ካገኘ ጥያቄውን ላይቀበለው ይችላል፡፡

4. የታክስ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የቀረበውን ሀሳብ በተናጠል ወይም በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 ሐ ላይ ከተጠቀሱት አገር/አገራት ጋር በመመካከር ሊቀበለው ይችላል፡፡

5. የታክስ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በግብር ከፋዩ የቀረበውን ሀሳብ ከተቀበለ ወይም ከግብር ከፋዩ ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት ማስተካከያ በሚድረግ ግብር ከፋዩ ስምምነቱን በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ እስካዋለ ድረስ በስምምነቱ ወስጥ በሚከተቱ ግንኙነቶች ላይ በአንቀጽ 4(2)ላይ የተቀመጠው የማስተላለፊያ ዋጋ ማስተካከያ እንደሚፈፀም መግለጽ ይኖርበታል፡፡

6. የግብይት ዋጋ የመወሰኛ ዘዴን ለመወሰን አስቀድሞ የሚደረግ ስምምነት በስምምነቱ ከሚሸከት ከ5 የታክስ ዓመታት ለሚበልጥ ጊዜ ፀንቶ የሚቆይ ሲሆን ስምምነቱ ከፀደቀ በኋላ በሚደረግ ቁጥጥር የሚደረግበት ግብይት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ተዋዋይ ወገኖች የስምምነቱ ወጤቱ ጥያቄ በቀረበበት በተያዘው የታክስ ዓመት ወይም ከዚህ የታክስ ዓመት በፊት ባሉ የታክስ ዓመታት ጭምር ተፈፃሚ እንዲሆን ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

7. ከላይ በላይ በንዑስ አንቀጽ 6 የተጠቀሰው ቢኖርም የታክስ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ፡-

   ሀ. ግብር ከፋዩ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ መረጃ የሰጠ ወይም ሚድረግ የሚገባውን ያላደረገ መሆኑን የተረዳ ወይም ግብር ከፋዩ በስምምነቱ ወስጥ የተቀመጡትን ሁኔታዎች ያላሟላ ከሆነ ወደኋላ ተፈፃሚነት ባለው ወጤቱ ስምምነቱን ሊሰርዘው ይችላል፡፡

   ለ. ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ መረጃ የሰጠው ወይም ሚድረግ የሚገባውን ያላደረገው ግብር ከፋዩ ያልሆነ እንደሆነ ወይም ግብር ከፋዩ ወሳኝ የሆኑ የስምምነቱን ቃሎችና ሁኔታዎች በበቂ ሁኔታ ያላሟላ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ወይም አንድ ወይም ከአንድ በላይ ለስምምነቱ ወሳኝ የሆኑት ግምቶች ተጥሰው የተገኙ እንደሆነ ወይም ስምምነቱ ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚያደርግ የሕግ ለወጥ የተደረገ እንደሆነ ስምምነቱ ለወደፊት ተፈፃሚ እንዳይሆን ሊሠርዝ ይችላል፡፡

8. የታክሱ ባለሥልጣን የግብይት ዋጋ የመወሰኛ ዘዴን አስቀድሞ ለመወሰን ለሚደረግ ስምምነት አጋዥ እንዲሆኑ የሚቀርቡ የንግድ ሚስጥሮችን እና ተጋላጭ የሆኑ ሌሎች መረጃዎችን እና ሰነዶች ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሀለት

## <u>በሌሎች ግብይቶች ላይ ስለሚፀረው ተፈፃሚነት</u>

### 13. <u>የአገልግሎት ግብይቶች</u>

1. ለዚህ መመሪያ ዓላማ ሲባል "አገልግሎት" ማለት፤ በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ ከአንድ ወል ጋር ወይም ሥራ እና እርዳታ ጋር ተያይዘው የሚሰጡ መብቶች፣ ጥቅሞች ልዩ መብቶችና አገልግሎቶች ሲሆኑ የገንዘብ ድጋፍንም ይጨምራል፡፡

2. የዚህ መመሪያ ሌሎች አንቀጾች እንደተጠበቁ ሆነው ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተደረገ የአገልግሎት ክፍያ ከገበያ ዋጋ ሚሆዎች ጋር የተጣጣመ ነው የሚባለው፡ -



Revi.Transf.dier.Amha.W/GT

ሀ) በእርግጥ ለተሰጠ አገልግሎት የተከፈለ ሲሆን፣

ለ) አገልግሎቱ የአገልግሎት ተቀባዩን የንግድ ደረጃ ከፍ በሚደረግ ኢኮኖሚያዊ ወይም የንግድ ጥቅም የሚሰጥ ወይም እንዲሰጥ የሚጠበቅ ሲሆን፣

ሐ) በተመሳሳይ ሁኔታ ወስጥ የሚገኝ ግንኙነት የሌለው ሰው ለሚሰጠው አገልግሎት ለመክፈል ፈቃደኛ ከሚሆነው ዋጋ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣

መ) የዋጋው ማጠን በተመሳሳይ ሁኔታ ወስጥ በሚገኙ ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች ተነጻፃሪ አገልግሎትን አስመልክተው ስምምነት ሊያደርጉበት የሚችሉ ሲሆን ነው፡፡

3. ለአንድ ሰው የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣመ ሊሆን የሚችለው ክፍያውን የፈፀመው ግንኙነት ያለው ሰው ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ አባላት በአክሲዮን ድርሻ ጥቅም ምክንያት የተከፈለ ሲሆን ነው፡፡ ሆኖም በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን የሚከተሉትን ወጪዎች ወይም ሥራዎች ይጨምራል፡-

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ ከተጠቀሰው ድርጅት እናት ኩባንያ ህጋዊ አቋም (አወቃቀር) ጋር ተያይዞ የሚወጣ ወጭ ለምሳሌ

ለእናት ኩባንያው ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ፣ የእናት ኩባንያውን አክሲዮኖች ለማዘጋጀትና ለእናት ኩባንያው ተቆጣጣሪ ቦርድ ወጭ፣

ለ) ሪፖርቶችን ማጠቃለልን ጨምሮ የእናት ኩባንያውን ሪፖርት የሚደረግ ግዴታ ለመወጣት የሚወጣ ወጭ ወይም የተከናወነ ድርጊት፣

ሐ) በአንድ የንግድ ሥራ ቡድን (Group) ወስጥ አባል የሆኑ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በቡድኑ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለሚከናወኑ ተግባራት የሚወጣ ወጪ ወይም ለዚህ ዓላማ ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚወጣ ወጪ ተቀባይነት የሚኖረው እነዚህ የቡድኑ አባላት አስቀድሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ወጪውን ባወጣው ሰው ባለቤትነት ስር ያልነበሩ ወይም እነዚህ ሰዎች በቡድኑ ወስጥ እንዲካተቱ የተደረገው ለዚህ ሰው ጥቅም ወይም ለወደፊት ለሚያገኘው ጥቅም ሲባል ካልሆነ ብቻ ነው፡፡

4. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ድንጋጌዎች እደተጠበቁ ሆነው፣ አንድ የተወሰነ አገልግሎት በአንድ ሰው ለሌላ ግንኙነት ላለው ሰው የተሰጠ መሆኑን ማሳየት (ማወቅ) የሚቻል ሲሆን፣ ለአገልግሎት የተከፈለው ክፍያ ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣመ መሆን አለመሆኑ የሚወሰነው እያንዳንዱን አገልግሎት በተናጠል በመውሰድ ይሆናል፡፡

5. አንድ ሰው አንድን አገልግሎት ለተለያዩ ግንኙነት ላላቸው ሰዎች የሰጠ እንደሆነና ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠውን የተወሰነ አገልግሎት ማሳየት ካልተቻለ ጠቅላላው የአገልግሎት ክፍያ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ

የድልድል ማሻ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ለእያዳንዱ ጥቅም ላገኘ ግንኙነት ላለው ሰው ይደለደላል፡፡ ለድልደላው መሠረት የሚሆኑት ቁልፍ ነጥቦችም፡ –

ሀ) የአገልግሎቶቹን ባህሪይና የተሰጡበትን ሁኔታ ከግምት ወስጥ ከማስገባት ጋር የተገናኙ፣

ለ) አገልግሎቶቹ ሊሰጣቸው የታሰቡት ወገኖች ያገኙትን ወይም ያገኛሉ ተብሎ የሚጠበቀውን ጥቅም ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ የሚገምቱ፣

ሐ) ማሉ በሙሉ ቁጥጥር ካልተደረገባቸው ግብይቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው፣

መ) ሚዛናዊና አስተማኝ በሆነ ሁኔታ ሊለኩ የሚችሉ መሆናቸውን ግምት ወስጥ ማስገባት፣ ይሆናሉ፡፡

## 14. የማይጨበጡ (ግዙፋዊ ህልዮት የሌላቸው) ንብረቶችን የሚመለከቱ ግብይቶች

1. ለዚህ መመሪያ ዓላማ ሲባል፣ ግዙፋዊ ህልዮት የሌላቸው ንብረቶች ግብይቶች የሚባሉት፣ በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ ፓተንትን፣ ኮፒራይትን፣ ቀመርን፣ ሂደትን፣ ዲዛይን፣ ሞዴል፣ ፕላን፣ የንግድ ምስጢር፣ ዕወቀትን፣ የንግድ ምልክትንና መሰል ንብረቶችን ማከራየትን፣ ማሻጥንና ሌላ ማንኛወንም ማስተላለፍን ወይም ወል ማድረግን የሚጨምሩ ናቸው፡፡

2. ግዙፋዊ ህልዮት የሌላቸውን ንብረቶች በተመለከተ የሚደረጉ ቁጥጥር የተደረገባቸው ግብይቶች ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለመወሰን የሚቻለው ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ለግብይቱ ያላቸውን አስተያየት (አመለካከት) በተለይም ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገኙ ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች ሊቀበሉት የሚፈቅዱበትን ዋጋ ግምት ወስጥ በማስገባት ነው፡፡

3. የዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ድንጋጌዎች ግዙፋዊ ህልዮት በሌላቸው ንብረቶች ግብይቶች ላይ ተግባራዊ ሲደረጉ ቁጥጥር ያልተደረገባቸውን ግብይቶች ለማነጻፀር ልዩ ሁኔታዎች ታሳቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም ልዩ ሁኔታዎች በእነዚህ ብቻ ሳይወሰኑ የሚከተሉት ናቸው፡፡

   ሀ) ግዙፋዊ ህልዮት ከሌለው ንብረት ይገኛል ተብሎ የሚጠበቀው ጥቅም፣

   ለ) ግዙፋዊ ህልዮት በሌለው ንብረት መብት ማጠቀም ላይ የሚጣል ማንኛወም ጂኦግራፊያዊ ገደብ፣

   ሐ) የሚተላለፈው መብት ብቸኛ መብት መሆን ወይም አለመሆን፣

   መ) መብቱ የሚተላለፍለት ሰው አስተላላፊው በንብረቱ ላይ ተጨማሪ ወጪ ሲያወጣ የመካተፍ መብት ያለው መሆን አለመሆኑ፣

# ክፍል ሦስት
# ስለሠነድ አያያዝ

## 15. የማስተላለፊያ ዋጋን ለመወሰን የሚያዝ ሠነድ

1. አንድ ታክስ ከፋይ በሚሟላከተው የታክስ ዘመን የተደረጉ ቁጥጥር የተደረገባቸው ሁኔታዎች ከገበያ ዋጋ ሚዛን ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ወቅታዊ ሰነድ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ሠነድ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ) የታክስ ከፋዩን የንግድ አሠራር አጠቃላይ ዳሰሳ (ማለትም ታሪኩን፣ የቅርብ ዕድገቱን ወይም አመጣጡን እና አጠቃላይ የገበያዎች ማነፃፀሪያ) እና ድርጅታዊ ቻርት (ማለትም የንግዱን አሃዶች (ዩኒትስ)) መምሪያዎች እና ድርጅታዊ መዋቅሩን፣

ለ) ታክስ ከፋዩ አባል የሆነበትን ቡድን ድርጅታዊ መዋቅር (ሁሉንም የድርጅቱ አባላት፣ ህጋዊ አቋማቸውን ፣ የአክሲዮን መቶኛ ድርሻቸውን) እና የቡድኑን የአሠራር መዋቅር (የቡድን ሥራዎች በሚሟላከት እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ቁጥጥር የተደረገበትን ግብይት በሚሟላከት የሚያከናውነውን ተግባር የሚያሳይ ማብራሪያ፣)

ሐ) በአንቀጽ 5 የተዘረዘሩትን የማነጻፀሪያ ሁኔታዎች ጨምሮ ቁጥጥር የተደረገባቸውን ግብይቶች የሚሟላከት ማብራሪያ፣

መ) የበለጠ ተስማሚ የሆነውን የማስተላለፊያ ዋጋ ለመወሰን ጥቅም ላይ የሚውለውን ዘዴ(ዎች) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማነፃፀሪያነት የሚያገለግለው ወገንና የፋይናንስ ጠቋሚ እንዴት እደተመረጡ የሚያሳይ ማብራሪያ፣

ሠ) የንጽጽሮሽ ትንተና ማለትም ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶችን ለማየት የተከናወነውን ሂደት የሚያሳይ ማብራሪያ፣ ማንኛውም የወደፊት ወስጣዊ ተነጻጻሪ ግብይት እንዴት ተቀባይነት እንዳጣ የሚያሳይ ማብራሪያ (አስፈላጊ ሲሆን)፣ ተነጻጻሪ የሆኑ ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ግብይቶችን የሚሟላከት ማብራሪያ፣ ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ግብይቶችን የሚሟላከት ማብራሪያ፣ ቁጥጥር የተደረገባቸው ግብይቶችን እና ተነጻጻሪ የሆኑ ቁጥጥር ያልተደረገባቸውን ግብይቶች የሚሟላከት ትንተና (አንቀጽ 5ን ግምት ወስጥ በማስገባት) እንዲሁም የንጽጽሮሽ ዋጋ ማስተካከያዎች የተደረገበት ዝርዝር ማብራሪያ፣

ረ) ለማንኛውም ኢንዱስትሪያዊና ኢኮኖሚያዊ ትንተና መሠረት የተደረጉ በጀቶችና የወደፊት ግምቶች፣

ሰ) ቁጥጥር የተደረገባቸውን ግብይቶች በሚመሟላከት ዋጋን አስሜልክቶ በሌሎች ሀገሮች የሚደረጉ ስምምነቶችን የሚሟላከት ዝርዝር፣

ሸ) ቁጥጥር የተደረገባቸው የግብይት ሁኔታዎች ከገበያ ዋጋ ሚዛን ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለሚረጋገጥ የተደረጉ የዋጋ ማስተካከያዎች ማጠቃለያ (ሚያምሚያ)

ቀ) ቁጥጥር የተደረገባቸውን ግብይቶች በሚሟላከት ታክስ ከፋይ የገበያ ዋጋ ሚዛን የተከተለ መሆኑን ለመወሰን ጉልህ ተፅዕኖ የሚኖረው ሌላ ማንኛውም ሚጃ፣

3. ሰነዱ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሊቀርብ ይችላል፡፡

4. በአንድ የታክስ ዘመን የቀረበ ሰነድ ወቅታዊ ነው የሚባለው በሕግ በተደነገገው የታክስ ማስታወቂያ ጊዜ ወስጥ የቀረበ እንደሆነ ነው፡፡

5. በታክስ ባለሥልጣኑ የጽሑፍ ጥያቄ በቀረበ በ45 ቀናት ወስጥ ሰነዱ ለታክስ አስገቢው ባለሥልጣን መቅረብ ይኖርበታል፡፡

6. የታክስ ባለሥልጣኑ በአዲት ሥርዓት አሠራሩን ሚጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሚጃ የመጠየቅ ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የታክስ ከፋዩ ይህንን ሰነድ የመቅረብ ግዴታው ሁልጊዜም የፀና ነው፡፡

## ክፍል አራት
## <u>አስተዳደራዊ ሥነ-ሥርዓቶች</u>

### 16. <u>ለሀገር ወስጥ ግብይቶች የሚደረጉ ተመሳሳይ የዋጋ ማስተካከያዎች</u>

በገቢ ግብር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 286/1994) አንቀጽ 29(1) መሠረት የታክስ ባለሥልጣኑ በታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበት የሀገር ወስጥ ግብይት ላይ የዋጋ ማስተካከያ ሲያደርግ፣ ከዚህ ታክስ ከፋይ ጋር ግብይት ባደረገወን ወገን ታክስ በሚከፈልበት ገቢም ላይ ተገቢወን የዋጋ ማስተካከያ ሚድረግ ይኖርበታል፡፡

### 17. <u>ለዓለም አቀፍ ግብይቶች የሚደረጉ ተመሳሳይ የዋጋ ማስተካከያዎች</u>

1. የታክስ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበወን አቤቱታ መሠረት በሚድረግ ማስተካከያው ከገበያ ዋጋ ሚህ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለሚጋገጥ ምርመራ ሊያደርግ የሚችለው፡-

   ሀ) ቁጥጥር የተደረገበት ግብይት ሁኔታዎች በሌላ ሀገር የታክስ አስተዳደር ማስተካከያ ሲደረግባቸው፣

   ለ) በሌላ ሀገር የተደረገው የዋጋ ማስተካከያ ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት አባል የሆነው ወገን በዚያው ሀገር ከግብይቱ ባገኘው ትርፍ ማጠን ታክስ እንዲከፍል የሚያደርግ ወጤት የሚኖረው ሆኖ፣ ይኸው ታክስ ከፋይ በኢትዮጵያም ታክስ ከፋይ በመሆኑ ምክንያት ታክስ እንዲከፍል የተደረገ ሲሆን፤

   ሐ) የዋጋ ማስተካከያው እንዲደረግ ሀሳብ ያቀረበው ሀገር ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት የሚያስችል ስምምነት ከኢትዮጵያ ጋር የተፈራረመ ከሆነ፣ሲሆን፣ ታክስ አስገቢው ባለሥልጣን የዋጋ ማስተካከያው በሚህም ሆነ በማጠን ከገበያ ዋጋ ሚህ ጋር የተጣጣመ ነው የሚል ሚደምደሚያ ላይ ከደረሰ ከታክስ ከፋዩ ላይ በሚፈልገው የታክስ ማጠን ላይ ተገቢወን ማስተካከያ ያደርጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበው የዋጋ ይስተካከልልኝ አቤቱታ የታክስ ባሰሥልጣኑ በወጭ ሀገር የተደረገው ማስተካከያ ከገበያ ዋጋ ሚህ ጋር የተጣጣመ መሆኑን

ለመወሰን ከሚያስፈልገው መረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ይህም መረጃ የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

ሀ) ግንኙነት ያለዉን ሰው ስም፣ የተመዘገበ አድራሻ፣ አግባብነት ሲኖረው ግንኙነት ያለዉን ሰው የንግድ ስም (ስሞች)

ለ) ግንኙነት ያለዉን ሰው የታክስ አድራሻ የሚያሳይ ማስረጃ፣

ሐ) የተስተካከለው ቁጥጥር የተደረገበት ግብይ የተከናወነበትን ዓመት (ዓመታት)፣

መ) የተጠየቀው ተመሳሳይ የዋጋ ማስተካከያ እና በውጭ ሀገር የታክስ አስተዳደር መ/ቤት ማስተካከያ የተደረገበት የገንዘብ መጠን፣

ሠ) በሌላው ሀገር የተደረገውን ማስተካከያና ማስተካከያው በምን ላይ ተመስርቶ እንደተደረገ፤ እንዲሁም የንጽጽሮሽ ትንተና የተደረገበትን መሻሻና ተግባራዊ የተደረገውን የማነጻገሪያ ዋጋ ዘዴ የሚያሳይ ማስረጃ፣

ረ) ግንኙነት ያለው ሰው በሌላው ሀገር የታክስ ባለሥልጣን የተደረገውን የዋጋ ማስተካከያ ሊያስቀንስ ወይም ሊያሸር የሚያስችለው አቤቱታ አለማቅረቡን ወይም ሊያቀርብ አለመቻሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

2. አቤቱታው መቅረብ የሚኖርበት ተፈፃሚነት ባለው የታክስ ስምምነት ወስጥ አንድ ጉዳይ በጋራ ስምምነት ላይ ተመስርቶ እልባት ሊያገኝ ይችል ዘንድ ጥያቄ ሊያቀርብ በሚቻልበት የጊዜ ገደብ ወስጥ ነው፡፡

## 18. ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት (OECD) የማስተላለፊያ ዋጋ ለመወሰን ያወጣው መመሪያ አግባብነት

የዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት ደንበር-ዘለል ድርጅቶችን አስመልክቶ ያወጣው የማስተላለፊያ ዋጋን ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ ይህንን መመሪያ ለመተርጎም እንደ ዋነኛ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሆኖም ግን የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት መመሪያ ከገቢ ግብር አዋጁና ከዚህ መመሪያ ጋር የሚጋጭ ሲሆን የገቢ ግብር አዋጁና ይህ መመሪያ የበላይት ይኖራቸዋል፡፡

## 19. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ማንኛውም መመሪያ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ከሆነ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 20. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ጥቅምት 1, 2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ __________ ቀን 2007 ዓ.ም*

*ሱፍያን አህመድ*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት*
*ሚኒስትር*